# “እንኳኩ ይከፈትላችኋል፣ እሹ ታገኛላችሁ”

ርእሰ አንቀጽ፣ የግንቦት 7 ድምጽ፣ ቁጥር 32 ታህሣሥ 16 2001

በምእራቡ አለም ያሉ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ልደተ በአል በዛሬው ዕለት ያከብራሉ። ለበአሉም ባላቸው ከፍተኛ አክብሮት፣ የቅርብ ወዳጅ ዘመዶች ስጦታ ይለዋወጣሉ። አሰሪዎች ለሰራተኞቻቸው ግብዣ ያደርጋሉ፣ ድርጎም ይሰጣሉ። ነጋዴዎች ከአመቱ ገቢያቸው ሩቡን ያህል በገና ወቅት ያገኛሉ። የደስታ ወቅት ነው። ለዚህ ሁሉ ስጦታ፣ ምስጋናና፣ ደስታ ምክንያቱም፣ የምእራብ ክርስቲያኖች በኢየሱስ መወለድ የሰው ልጅ ከፈጣሪው የሚጋራው ቅድስናና ክህሎት የተላበሰበት፣ ህይወቱ ከእንስሳነት ወደ ሰብእና ያረገበት፣ በሰብእናውም ውዳሴ ክብርና ምስጋና የሚገባው መሆኑን የተቀበሉበት ዕለተ በአል ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ በመነሳቱ፣ ትንሳኤ ታላቁ በአላችን እንደሆነው ሁሉ፣ ለምእራባውያን ደግሞ፣ በምድረበዳ ሲንከራተት የነበረው ሰው በኢየሱስ ልደት የተነሳ፣ መንፈስ ቅዱስ ስጋ ለብሶ በሰዎች ዘንድ እንዲኖር ምክንያት በመሆኑ እጅግ አግዝፈው ያከብሩታል።

ታላቁ ፈላስፋቸው ሄግል “የአለሙ መንፈሳዊ ምስቅልቅል አንዳች መድህን በፈለገበት ቅፅበት አንድዬ ልጁን ላከ” ብሎታል። ምእራባውያን፣ የግል ህይወታቸውን ከፈጣሪ መንፈሳዊ ባህሪ የሚጋራ አድርገው ስለተቀበሉም፣ ከዚህ እምነታቸውም በመነጨ፣ ለህይወት የሚገባውን ቅድስናና ክብር የመስጠትን አመለካከቶች እንዲያዳብሩ ረድቷቸዋል። ለግለስብና ሰብአዊ መብቶች መከበር በሚያደርጉትም ትግል፣ ይህ መንፈሳዊ ሃይል ታላቅ ድጋፍ እንዳደረገላቸው እሙን ነው።

ባለፉት አርባ አመታት ወደነዚህ ምእራባውያን ሃገሮች የተሰደዱ ኢትዮጵያውያንም፣ ከሚኖሩባቸው ማህበረሰቦች እየተማሩ ለመሰረታዊ መብቶች ቀናኢ ሆነዋል። ለህይወት ክብርን መስጠትና፣ በእናት ሃገራቸው አምባገነኖች በሚደርሰው የህይወት ብካይ መንገብገብ መለያ ባህሪያቸው ሆኗል። በቁርና በሃሩር ይሰለፋሉ፣ ከባለስልጣናት ደጃፍ ሻማ እያበሩ ያመሻሉ፣ ለእመ ሃገራቸው ያነባሉ። በዘንድሮው የገና በአል ወቅት ደግሞ ከፍ ያለ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። አምባገነኖች ባስከፏቸው ቁጥር በሃሩሩና በቁሩ እየተጠበሱ ከሚያነቡና ከሚሰለፉ፣ የአምባገነንነትን መሰረት ለአንዴና ለሁልጊዜም መንግለው እንዲጥሉ ከግንቦት ሰባት ጥሪ ተደርጎላቸዋል። ወደዚህ የመጨረሻ ግብግብ ለመግባትም፣ ትግሉ የሚያስፈልገውን የዝግጅት እርዳታ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል።

ንቅናቄያችን ይህን መሰል ጥሪ ሲያደርግ በነደፈው ስልትና፣ በማደራጀት ላይ ባለው ህዝባዊ አቅም በመተማመን ነው። በዚህ በምእራባውያን የገና ሳምንት የሚወደሰውን የህይወት ቅድስናና ልእልና፣ በሃገራችንም ወንዞች ፈሶ፣ መስኖ ሆኖ የደረቀውን መሬታችንን አጠጥቶና አፈሩን አለስልሶ፣ በዚያ ላይ የሚያቆጥቁጠው ኢትዮጵያዊው ህይወት ከዚህ በፊት በአምባገነኖች ከተወረወረበት አቧራና ትቢያ እንዲነሳ፣ መታገል አማራጭ ያልተገኘለት በመሆኑም ጭምር ነው። ያለመስዋእትነት ነፃ የወጣ ህዝብ እንደሌለ ንቅናቄያችን አጥርቶ ያውቃል። በዘረኝነት በተለወሰ ስርአት ውስጥ ደግሞ፣ የገዢዎቻችን እብሪት ከእኛ አልገዛም ትንንቅ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን፣ ከአናሳነታቸው ከሚመነጭ ፍርሃት የሚቀፈቀፍ በመሆኑ፣ ስለፍቅርና መቻቻል እንኳ ስንዘምር፣ የሚያዳምጡት፣ መዝሙራችንን ሳይሆን፣ በስንኞቻችን መሃል ያነበቡትን የነርሱን ትርጓሜ (ፍርሃት) ለመሆኑ፣ የቴዲ አፍሮ እስራትና እንግልት በቂ ትምህርታችን ነው።

እንደ ምእራባውያን ለህይወት ክብር እንስጥ፣ በሰብእናችን ከፈጣሪያችን የምንጋራው ቅድስና አለ የምንልማ ከሆነ፣ የፈጣሪያችን ማደሪያ የሆነውን ሰብእናችንን ከይሲና እኩይ አላማ ላላቸው አምባገነኖች ተገዢ ልናደርገው አይቻለንም። ለህይወት ያለን ክብር እንድንሰየፍለት የሞራል ግዴታ ያሳድርብናል እንጂ። ይህን ከመሰለ ጥልቅ እምነትም በመነጨ ነው በዚህ የገና በአል ሳምንት የኢትዮጵያውያንን አበርክቶ ስንጠይቅ፣ ከራሱ ከልደት መንፈስ ጋርም የተዋደደና የተቆራኘ ነው የምንለው። በገና በአል የሚወደሰውን ቅዱስ ህይወትን ራሱን ከብካይ ለመከላከል የምናደርገው ስጦታ ስለሆነ ሁላችንም ደስ ልንሰኝበት ይገባል። ኢየሱስ ሲያስተምር “እንኳኩ ይከፈትላችኋል፣ እሹ ታገኛላችሁ” ብሏልና፣ በዘረኛ አምባገነኖች ከትቢያ ላይ የተወረወረውን ኢትዮጵያዊ ህይወት፣ የሚገባውን የክብር ቦታ ለመስጠት በህሊና ሃይላችን የሳልናትን እመ ሃገር ለማግኘት፣ ግንቦት 7 የኢትዮጵያውያንን የህሊና በር ማንኳኳት ጀምሯል። የወገኖቻችንም ምላሽ ከጅማሮው ከጠበቅነው በላይ እንደሆነ እያየነው ነው። ምስጋናችን እጅግ የላቀ ነው።

መልካም የልደት በአል!

የግንቦት 7 የፍትሕ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
www.ginbot7.org